ዘምዘም
ZamZam
Bank

## ዘምዘም ባንክ አ/ማ

## የመምሥረቻ ጽሑፍ ላይ የቀረበ የማሻሻያ ሃሳብ

1. ከዚህ በፊት በመምሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 4(2) ላይ ተጨማሪ ተግባራትና ዓላማዎች ከዚህ በታች እንደተመለከተው እንዲካተቱ በማድረግ ማሻሻያ ተደርጓል፡-

   “(አ) ተቀጽላ ድርጅቶችን ወይም እህት ማኅበሮችን በማቋቋም በተለያዩ የንግድ መስኮች ላይ መሰማራት፣”

   “(ከ) ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ ህንጻዎችን ገዝቶ መሸጥ፣”

   በዚሁም መሰረት ከዚህ ቀደም በመስረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 4(2) (አ) ላይ ተቀምጦ የነበረው ሃሳብ ምንም ለውጥ ሳይደረግበት ቅደም ተከተሉን ብቻ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ወደ ሚቀጥለው ተራ ቁጥር ፊደል ማለትም “ኸ” እንዲሸጋሸግ በማድረግ ብቻ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

   “(ኸ) ከላይ ከተዘረዘሩት ዓላማዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ማናቸዉንም ዓይነት የባንክ ሥራዎችን መሥራት፡፡”

2. ከዚህ ቀደም በመምሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 7 ላይ ከንዑስ ቁጥር 1-7 ድረስ የተመለከቱት አንቀጾች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተለው ተጨማሪ ንዑስ ቁጥር 8 ከዚህ በታች እንደተመከተው እንዲካተት በማድረግ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

   “(8) የባንኩ አክሲዮኖች በንግድ ሕግ አንቀጽ ቁጥር 272(2) መሠረት ጉዑዝ አልባ ሆነው ይወጣሉ፡፡”

3. ከዚህ ቀደም በመምሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 10 ላይ የአክሲዮን ሰርተፊኬን አስመልክቶ ከንዑስ ቁጥር 1 እስከ 3 ድረስ የተቀመጡት አንቀጾች ምንም ለውጥ ሳይደርግባቸው እንደተጠበቁ ሆነው ተጨማሪ ንዑስ ቁጥር 4 ከዚህ በታች እንደተመለከተው እንዲካተት በማድረግ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

   “(4) ሆኖም አግባብነት ያላቸውን ሕጎችን መሰረት ባንኩ በወረቀት የወጡትን አክሲዮኖች ወደ ጉኡዝ አልባ አክሲዮኖች እንዲተኩ በሚያደርግበት ወቅት በዚህ አንቀጽ ከቁጥር 1 እስከ 3 ድረስ የተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡”

4. በመምሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 14(ሐ) ተቆጣጣሪ ቦርድ የሚለው እንዲሰረዝ እና በተቀሩት ንዑስ ቁጥሮች ምንም ዓይነት ለውጥ ሳይደረግባቸው እንደሚከተለው እንዲሸጋሸጉ በማድረግ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

"የባንኩ አስተዳደር አካላት የሚከተሉት ናቸዉ ፡-

ሀ. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ፣

ለ. የዲሬክተሮች ቦርድ፣

ሐ. የሸሪዓ አማካሪዎች፣

መ. ዋና ስራ አስፈጻሚ፣

ሰ. የውጪ ኦዲተር፣ እና

ረ. የማኅበሩ ጸሐፊ"

5. ከዚህ ቀደም በመምሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 18(1) ላይ "ባንኩ የሚተዳደረው በባለአክሲዮኖች ጉባኤ የሚመረጡ 11(አስራ አንድ) አባላት ባሉት የዲሬክተሮች ቦርድ (ከዚህ በኋላ ቦርድ) ይሆናል በሚል የተቀመጠው ንዑስ አንቀጽ ተሰርዞ በሚመለከተው እንዲተካ ተደርጓል፡፡"

"18(1) ባንኩ የሚተዳደረው በባለአክሲዮኖች ጉባኤ የሚመረጡ 13(አስራ ሦስት) አባላት ባሉት የዲሬክተሮች ቦርድ (ከዚህ በኋላ ቦርድ) ይሆናል፡፡"

6. ከዚህ ቀደም በመምሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 21(4) ላይ "ከድንገተኛ ስብሰባ □ች የዲሬክተሮች ቦርት መደበኛ ስብሰባ ከማካሄዱ ከሦስት ቀናት በፊት ለቦርዱ አባላት በሰብሳቢው □□ም በማኅበሩ ጸሐፊ በኩል ጥሪ መደረግ አለበት፡፡.." በሚል ተቀምጦ የነበረው ተሰርዞ በሚከተለው እንዲተካ ተደርጓል፡፡

"(4) ከድንገተኛ ስብሰባ □ች የዲሬክተሮች ቦርት መደበኛ ስብሰባ ከማካሄዱ በፊት አግባብብነት ባለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ላይ በተመለከተው ዝቅተኛ የጊዜ ገደብ መሰረት ለቦርድ አባላት በሰብሳቢው □□ም በማኅበሩ ጸሐፊ በኩል አስቀድሞ ጥሪ መደረግ አለበት፡፡ □ሪ □ሚ□ረ□□ም □ስብሰባ□ን አጀንዳ በማያያዝ ለዲሬክተሮች በሙሉ በኢሜል ወይም በሌላ ኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በሚ□ርስ □□ሪ □ንሑአ ማስታወቂያ ይሆናል፡፡"

7. ከዚህ ቀደም በመምሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 21(6) ላይ “የዲሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሰብሳቢው እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡” በሚል ተቀምጦ የነበረው አንቀጽ ተሰርዞ በሚከተለው እንዲተካ በማድረግ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

“(6) የዲሬክተሮች ቦርድ መደበበኛ ስብሰባውን አግባብበነት ባለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ላይ በሚጠይቀው ዝቅተኛ የጊዜ ገደብ ውስጥ መደበኛ ስብሰባውን ማካሄድ አለበት፡፡ ሆኖም ሰብሳቢው እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።”

8. ከዚህ ቀደም በመምሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 25 ላይ የተቆጣጣሪ ቦርድን ስልጣንና ተግባር አስመልቶ የተቀመጠው አንቀጽ ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዝና እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ በዚሁም መሰረት በመመሥረቻ ጽሑፉ አንቀጽ ቁጥር 26-44 ተቀምጠው የነበሩት አንቀጾች እንደ ቅደምተክተላቸው ወደ አንቀጽ ቁጥር 25-43 እንዲሸጋሸጉ ተደርገዋል፡፡